**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡**

## አራተኛ ሳምንት - ምዕራፍ ሦስት

## *ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ክብርና፣ አማላጅነት*

**ጥያቄ፡-** የድንግል ማርያም እናትና አባት ማን ይባላሉ?

**መልስ፡-** አባቷ ኢያቄም፣ እናቷ ሐና ናቸው፡፡

**ጥያቄ፡-** ስለ ድንግል ማርያም ልደትና አስተዳደግ በመጠኑ ቢነግሩን?

**መልስ፡-**

ከላይ እንደተናገርሁት የድንግል ማርያም እናትና አባት ኢያቄምና ሐና ይባላሉ፡፡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ እስራኤላውያን ነበሩ፡፡ ኢያቄም ከዳዊት ዘር ነበር ሐና ደግሞ ከአሮን ዘር ነበረች፡፡ ልጅ ስላልነበራቸው እያዘኑ ይኖሩ ነበር፡፡ በተለይም በአገራቸው ባህል መካንነት የኃጢኣት ምልክት እንደሆነ ስለሚቆጠር እግዚአብሔር የጠላቸው መስሏቸው ነበር፡፡ ወደ ሰሎሞን ቤተ መቅደስም ለጸሎት በሚሄዱበት ጊዜ በመካንነታቸው ብቻ የአቀባበል ልዩነት ይደረግባቸው ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ እያዘኑ ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ስዕለት ተሳሉ፡፡ ይኸውም ወንድ ልጅ የወለድን እንደሆነ ካህን ሆኖ ቤተ መቅደስን የሚያገለግል፣ ሴት የወለድን እንደሆነ መሶበ ወርቅ ሰፍታ፣መጋረጃ ፈትላ ለነዋየ ቅድሳት የምታቀርብ ልጅ ለእግዚአብሔር እንሰጣለን ብለው ነው፡፡ እግዚአብሔርም ስዕለታቸውን ሰምቶ ድንግል ማርያምን ወለዱ፡፡ ሦስት ዓመት ሲሆናት ቃላቸውን ጠብቀው ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ለሊቀ ካህኑ አስረከቧት፡፡ የመላዕክትን ዝማሬ እየሰማች መላዕክት እየመገቧት ቤተ መቅደስ እያገለገለች አሥራ ሁለት ዓመታት በቤተ መቅደስ ኖረች፡፡ በናት በአባቷ ቤት ከቆየችበት ሦስት ዓመት ጋር ሲደመር የአስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ነበራት፡፡ እድሜዋ አስራ አምስት ዓመት ሲሆን ሊቀ ካህናቱ የሀገር ሽማግሌዎችን ሰብስቦ ዕጣ አወጣ ዕጣው ዮሴፍ ለተባለ ሽማግሌ ወጣ፡፡ የእግዚአብሔር ገንዘብና ናትና ዮሴፍ በታማኝነት ሞግዚት ሆኖ እንዲጠብቃት ሆነ፡፡ በዮሴፍ ቤት ሆና ለቤተ መቅደስ መጋረጃ ስትፈትል የእግዚአሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መጥቶ እየሰገደ ሰላምታ ሰጥቶ አምላክ ከሷ በድንግልና የሚወድ መሆኑን ከእግዚአብሔር የተነገረውን ቃል ሳይለውጥ ነገራት፡፡ እሷም በሰላምታው ሳትመሰጥ ነገሩን በአዕምሮዋ አገላብጣ በመመርመር ቅዱስ ገብርኤልን ተገቢ ጥያቄ ጠየቀችው፡፡ ይኸውም «ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል» የሚል ነው/ ሉቃስ 1÷34፡፡/ ገብርኤልም መልእክቱን እንድትቀበለው በመጨነቅ ብዙ ምሳሌዎችን ጠቀሰላት፡፡ በመጨረሻም «ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም» አላት፡፡ የእግዚአብሔርን ስም ስላነሳ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ መሆኗን «እነሆ የእግዚአብሔር ባሪያ እንደ ቃልህ ይኹንልኝ፡፡» በማለት ድንግል ገለጠችለት፡፡ ወዲያኑም ወልደ እግዚአብሔርን በድንግልና ጸነሰች ከዘጠኝ ወር በኋላ በድንግልና ወለደችው፡፡

ድንግል በቤተልሔም ጌታን ስትወልድ በቤተ መንግስት ወይም በሚያምር እልፍኝ ውስጥ አልነበረም፤ በዋሻ ውስጥ ነበር እንጂ፡፡/ ሉቃስ 2÷7፡፡/ ልብስም ስላልነበራት በአሮጌ ጨርቅ ጠቀለለችው በበረት ውስጥ ከልጇ ጋር እንዳለች የሚበላ ነገር እንዳለ እንደሌለ እግዚአብሔር ብቻ ነበር የሚያውቀው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሥጋ በኩል ችግር መኖሩን ማደሪያ መጥፋቱን ሳይሰውር ነገሮናል፡፡በመንፈስ ግን ብዙ ታይተው የማይታወቁ ሁኔታዎችን ድንግል ማርያም አይታለች፡፡

ሀ. የመላዕክትን ቅዳሴ ሰምታለች፣

ለ. የእረኞችን ጭፈራና ደስታ አይታለች፣

ሐ. የጥበብ ሰዎች ያመጡትን እጅ መንሻ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ተቀብላለች፡፡

ድንግል ማርያም ጌታን ከወለደች በኋላ ሄሮድስ እንዳይገድልባት ወደ ግብጽ ይዛው ተሰዳለች፡፡ ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ የስደት ዘመን በኋላ ወደ ምድረ እስራኤል ተመልሳ አብረው ቆይተዋል፡፡ በማስተማር ጊዜውም እየተከራተተች ተከትላዋለች፡፡ የማስተማር ጊዜውን ጨርሶ በመስዋዕትነት በመስቀል ሲሰቀል እያለቀሰች ከመስቀሉ ሥር አልተለየችም፡፡ ከመስቀሉ ሥር እያለቀሰች ቁማ ባያት ጊዜ አሳዝናው እንዲጠብቃት ለዮሐንስ አደራ ሰጠው፡፡ ከትንሣኤው በኋላ ከሐዋርያት ጋር አብራ በመጸለይ በኢየሩሳሌም ሰንብታለች፡፡/የሐዋ.ሥራ 1÷14፡፡/ ኋላም ከዮሐንስ ጋር ወደ ኤፌሶን ሄዳ ከኤፌሶንም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ በ64 ዓመቷ አርፋ ወደ ልጇ ሄዳለች፡፡ ድንግል ማርያም የተቀበረችው በጌቴሴማኒ ነው፡፡/የሮማ ካቶሊኮችግን በኤፌሶን ነው ይላሉ፡፡/ ድንግል ማርያም በመቃብር አልቀረችም፡፡ በልጇ ፈቃድ ከመቃብር ወጥታ አሁን በልጇ ዘንድ ነው ያለችው፡፡ የድንግል ማርያም ታሪክ ባጭሩ ይህ ነው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡-

***ሀ/ ወላዲተ አምላክ ናት***

*ማቴ.*1.23 *«እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል» አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ሲሆን እግዚአብሔር በመንፈስ ረድኤት ሳይሆን በመንፈስ ልደት /በምሥጢረ ሥጋዌ/ ከእመቤታችን በተዋሐደው ሥጋ ከምእምናን ጋር መዋሐዱን ያመለክታል፡፡ የአዲስ ኪዳን የድኅነት መሠረትም ይኸው ነው፡፡*

### ለ. ከፍጡራን ልዩ ናት

የፍጡራን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴአቸው በሕገ ተፈጥሮ የተወሰነ የተገደበ ነው። ምክንያቱም መዓልት ሌሊት አይሆንም ሌሊትም መዓልት አይሆንም እናት ድንግል አትሆንም ድንግልም እናት አትሆንም። የእመቤታችን የታሪክ አጀማመርም ሆነ አጨራረስ ከላይ ከተመለከትነው ሕገ ፍጡራን የተለየ መሆኑን አባቶቻችን መስክረዋል። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የምሥራቹን ባቀረበበት ወቅት ከእመቤታችን በኩል የችኮላና የይሁንታ መልስ አላገኘም። ሉቃ.1፡31-44፡ ሉቃ. 2፡41-51 ይልቁንም «ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? » የሚል ሲሆን የማሳመኛ መልሱም ዮሴፍ እጮኛሽ አለ የሚል ሳይሆን «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል» የሚል ነበር። እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ ደግ ነገርና ደጋጐች ካሉበት ሁሉ ሊመጣ ይችላል። የምሥራቹ ማሰሪያ ግን «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» የሚለው ነው። እውነትም በድንግልና መኖር፣ በድንግልና መውለድና ከዚያም እንደገና በድንግልና መኖር ከሁሉም በላይ የአምላክ እናት መሆኗ ከፍጡራን በላይና ከፍጡራንም የተለየች መሆኗን ያስረዳል። «በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ።» ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው። ሕዝ.44.1። «ወይቤለኒ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ዛቲ አንቀጽ ዕፁት ይእቲ ወኢትትረኃው። - አንተ የባለ አእምሮ የአዳም ልጅ ይች በር ተዘግታ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም» በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል በምሳሌ አስረድቷል።

### ሐ. የአዲስ ኪዳን መነሻና መድረሻ ናት

አዲስ ኪዳን ማለት አዲስ ዘመን፣ አዲስ ሕይወት አዲስ ሥርዓት ከብዙ የልዩነትና የመርገም ዓመታት በኋላ ሰውና እግዚአብሔር በእርቅና በድኅነት በሰላም የተገናኙበት የተለየ የኪዳን ዘመን ነው። ይህ ሁሉ መልካም ነገር ደግሞ መጀመሪያ አለው እርሷም ወላዲተ አምላክ ናት። ታላቁ አባት ቅዱስ ቄርሎስ በድርሳኑ እንደመሰከረው «ገና ሰው ሳይሆን እንኳን ንዑድ ክቡር ገብርኤል ማርያም ሆይ አይዞሽ አትፍሪ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም አማኑኤል ትይዋለሽ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ብሎ ለድንግል ነገራት በማለት ጽፏል።» መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው ከመሆኑ በፊት መልአኩ ለእመቤታችን ያበሠራት መወለዱን ብቻ አይደለም።

1. **የሚወለድበትን ዓላማ ገልጦላታል፡** ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል ማለት በወቅቱ የሚጠበቅ ምሥጢር ነበር።

2. **ማን እንደሚወለድ ገልጦላታል፡** ስሙንም አማኑኤል ትይዋለሽ ማለት አምላክ ከአንቺ ሰው ለመሆን ፈቃደኛ ነው በማለቱ የዘመኑን መልካምነት ገልጦላታል።

3. **አይዞሽ አትፍሪ** ማለቱም የአዲስ ኪዳን ዘመን ፍርሃትና ድንጋጤ ተወግዶ በምትኩ መጽናናትና መረጋጋት የሰፈነበት ዘመን እየመጣ እንደሆነና ለዚህ ሁሉ ክንውንም ምክንያቱ እርሷ እንደሆነች መነሻውም መድረሻውም በእርሷ በኩል መሆኑን ስንመለከት እመቤታችን የአዲስ ኪዳን መነሻና መድረሻ ናት መባሉ እውነት ነው። ሉቃ.1፡30 «ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ።» እንዲል የአዲስ ኪዳን መድረሻም መንግሥተ ሰማያት ነው። የአዳም ልጆች መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የበቁትም በክርስቶስ ሰው መሆን ብቻ ነው። ታላቁ አባት ቅዱስ ኤፍሬም «በሔዋን ምክንያት የገነት በር ተዘጋ በእመቤታችን ምክንያት /በክርስቶስ ሰው መሆን/ ዳግመኛ ተከፈተልን» ብሏል።

**ጥያቄ፡-** ስለ ድንግል ማርያም አማላጅነት ደግሞ ቢያስረዱን?

**መልስ፡-** በመሰረቱ ማማለድ ለሌላው ተወክሎ ጉዳይ ማቅረብና ማስፈጸም ማለት ነው። ይህ አማላጅ በሁለቱም መካከል ታማኝነትና ወዳጅነት ያለው መሆን አለበት። ይልቁንም በተማላጁ ዘንድ ሞገስ ያለው መሆን አለበት። አማላጅ የሚልከውም ሰው በአማላጁ ላይ እምነት ስለጣለበት ርኅራኄውንም ስለሚያውቅ ከተማላጁ ጋር ያለው የፍቅር ግንኙነትና ሞገስ ስለሚያውቅም ነው አማላጅ የሚልከው። ስለምልጃ ስንናገር ሌሎች እንደሚሉት እግዚአብሔርን ጨካኝ ማድረጋችን ፍጡራንን ከእግዚአብሔር የሚበልጡ ርኅሩኆች ናቸው ማለታችን አይደለም። ሰውን ለማዳን የሚጠየቀውን ጥያቄ እግዚአብሔር ደስ ብሎት የሚቀበል መሆኑን ስለምናውቅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር በምልጃ የሚምር አምላክ መሆኑን ይነግረናል። ለምሳሌ፡- አምላኩን በጣዖት ለውጦ ሲሳሳት የነበረውን የእስራኤል ሕዝብ ሙሴ ጸልዮ አድኗል።/ ዘጸአት 32÷9-14/ ራሱን ሙሴን በከንቱ ስታማ የነበረችው እህቱ ማርያም በእግዚአብሔር ቁጣ በለምጽ በተለበለበች ጊዜ ሙሴ የምልጃ ጸሎት ጸልዮ አድኗታል።/ /ዘኁል 12÷1-15/ የእግዚአብሔር መዓት ፡ ሰይፍ የተመዘዘበትን የእሥራኤል ሕዝብ ዳዊት ጸልዮ መስዋዕትም ሰውቶ አድኗቸዋል።/ ሳሙ ካልዕ 24÷17-25/ ሮማዊው የወታደር አለቃ ለሰው መዳን ሲል ሲጨነቅ አይቶ ጌታ አሞገሰው አደነቀውም ምልጃንውን ተቀብሎ የቤት አሽከሩን አዳነለት።/ ማቴ 8÷5-13/ ጌታ ለማዳን የመጣ መሆኑን ሰምታ እየገሰገሰች መጥታ ስለልጇ ስቃይና አስከፊ ሕመም የነገረችው የሶርያዊው የፊንቄ ተወላጅ የሆነችው ሴት ለልጇ አማላጅ ሆና ልጇን አድናለች።/ ማቴ 15÷ 21-28/ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ አሠራር ይወዳል የራሱን ርህራኄ የሚመስል ርኅራኄ በሰው ዘንድ እንዲያይ ይፈልጋል። ስለዚህ ነው በቅዱስ መጽሐፍ የቀረቡ ምልጃዎች ሁሉ ቶሎ መልስ የተሰጣቸው። ከዚህ በላይ ያሳየናቸው ቦታዎች ለምሳሌ ያህል ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታዎች የምልጃን ትምህርት ያስተምራል። እንግዲህ ስለ ድንግል ማርያም አማላጅነት በቤተ ክርስቲያናችን የምናስተምረውም ከዚህ ተነስተን ነው። በልጇ ፊት ታማልዳለች። /እመቤታችን በዓመት ውስጥ 33 የመታሰቢያ ቀኖች አሏት። ከመባቻ ጀምሮ ስንቆጥር በየወሩ በ21ኛው ቀን የእመቤታችን ዕለት ነው። በዚህ ቀን ቅዳሴ ይቀደሳል ዝክርና ማኅበር ይጠጣል ጸሎተ ማኅሌት ይደርሳል።/

**ይቆየን።**